አማርኛ أمهرية

# 3 የተውሒድ ክፍሎች

የላቀውን አሏሁ ሱብሓነሁ ወተዓላን በጌትነቱ፣ በተመላኪነቱ እንዲሁም በስምና መገለጫዎቹ መነጠል

አይነቶቹ 3 ናቸው

## በጌትነቱ መነጠል

እሱም:- የላቀውን አላህ በስራዎቹ መነጠል ወይንም አላህን በፈጣሪነቱ፣ በንግስናው እንዲሁም በአስተናባሪነቱ መነጠልማለት ነው።

## በተመላኪነቱ መነጠል

እሱም:- የላቀውን አላህ በአምልኮ መነጠል ማለት ነው

## በስምና መገለጫዎቹ መነጠል

እሱም:- የላቀው አሏሁ ሱብሓነሁ ወተዓላ በኪታቡ ራሱን በገለፀባቸው እንዲሁም በነብያችን ምላስ ባወረዳቸው ስምና መገለጫዎች ያለምንም ማንሻፈፍ፣ ውድቅ ሳናደርግ፣ ከፍጡራን ጋር ሳናመሳስል እንዲሁም ሁኔታውን ሳንፈላሰፍ ለራሱ ባፀደቀው መልኩ በማፅደቅ መነጠል ማለት ነው።

# የዲን ደረጃዎች 3 ናቸው

## ኢስላም

እሱም:- ለሃያሉ አላህ በተውሒድ እጅ መስጠት፣ በመታዘዝ መንተት፣ ከሽርክ እና ከባለቤቶቹ ምፅዳት ነው።

### የእስልምና ማእዘኖች 5

1. ሁለቱ ምስክሮች(ሸሃዳዎች)
2. ሶላትን መስፈርቷን ጠብቆ መስገድ
3. ዘካህ መስጠት
4. የረመዷንን ወር መፆም
5. ሓጅ ማድረግ(ለቻለ ሰው)

## ኢማን

ኢማን ማለት በምላስ የሚነገር፣ በቀልብ የሚቋጠር፣ በሰውነት አካሎቻችን የሚተገበር፣ አልህን በመታዘዝ የሚጨምር፣ አላህን በማመፅ ደግሞ የሚቀንስ የዲን ክፍል ነው።

### የኢማን ማእዘኖች 6

1. በአላህ ማመን
2. በመላኢኮች ማመን
3. ባወረዳቸው መፅሓፍቶች ማመን
4. በላካቸው መለክተኞች ማመን
5. በመጨረሻው ቀን(የውመል ቂያማ)ማመን
6. መልካም ሆነ መጥፎ በአላህ ውሳኔዎች (በቀደር) ማመን

## ኢሕሳን

ኢሕሳን ብሎ ማለት የላቀውን አላህ ልክ እንደምታየው ሆነህ ልታመልከው ፤ ይህ ቢያቅትህ እንኳን እሱ እንደሚያየህ አውቀህ ልታመልከው ነው።

### አንድ ማእዘን በውስጡ ሁለት ደረጃዎች ያሉት

1. ዒባደቱል ሙሻሃዳህ
አላህን ልክ እንደምታየው ሆነህ ማምለክ
2. ዒባደቱል ሙራቀባህ
ባታየው እንኳን እንደሚያይህ ማወቅ

# 4 የሓራም ክፍሎች

## ትንንሽ ወንጀሎች

ከትላልቅ ወንጀሎች ያነሱ ናቸው። ትልልቅ ወንጀሎች ቢስቲግፋር (በተውበት) ይማራሉ። ትንንሾቹ ወንጀሎች ስናዘወትራቸው ወደ ትልልቅ ወንጀል ይቀየራሉ። ነብያችን ሰለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል:- አደራቹሁን ትንንሽን ወንጀሎች ራቁ ትንንሽ ወንጀሎች ተሰብሰበው ሰውየውን ያጠፉታልና።

## ትላልቅ ወንጀሎች

እንደ ድግምት፣ ወላጆችን ማመፅ፣ ወለድ መብላት፣ አስካሪ መጠጦች፣ መስረቅ፣ ሃሜት፣ ነፍስ ማጥፋት፣ የየቲሞችን ገንዘብ መብላትና የመሳሰሉት ባጠቃላይ የራሳቸው የሆነ ቅጣት የተዘጋጀላቸው ወንጀሎችን በሙሉ ያካትታል

## ትንሹ ሽርክ

አላህና አንተ ከፈለጋቹህ ማለት፣ ከአላህ ውጭ በሌላ አካል መማል፣ ትንሽ የሆነ ይዩልኝ፣ ተሚማ ማንጠልጠል፣ በገድ ማመን፣ መዳፍ ማስነበብ እና የመሳሰሉትን ለመጥቀም ወይንም ደግሞ ጉዳትን ለማስወገድ ሰብብ ይሆናሉ ብሎ ማመን ይህ አይነት ሽርክ ከእስልምና አያስወጣም ግን ከታላላቅ ወንጀል ውስጥ ይመደባል።

## ትልቁ ሽርክ

ለአላህ ቢጤ ማድረግ፡ ልክ አላህን እንደሚለምነው ሌላን አካል መለመን ወይንም አላህን እንደሚፈራው ሌላን አካል መፍራት፣ ወይንም አላህን እንደሚወደው ሌላን አካል መውደድ ወይንም ደግሞ ከዒባዳዎች አንዱን አንስቶ ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት። ይህንን ነገር የፈፀመ ከእስልምና ይወጣል በዚህ ላይ ሳይቶብት ከሞተ ደግሞ ጀሃነም ውስጥ ዘውታሪ ይሆናል።

sarhaan.com
mahadsunnah.com